# የወቅቱ የኢትዮጵያ የፖለቲካ፥ ማህበራዊ፥ ኢኮኖሚያዊ፥ ዲፕሎማሲያዊና ሌሎችም ተዛማጅ ሁኔታዎች

## ክፍል አንድ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ፥ እያንዳንዱ ዜጋም በተናጠል፥ በተፈጠሮ ባለሙሉ ነፃነት ነውና እንደ ሕዝብም እንደግለሰብም የእሱነቱ መግለጫው የሆነውን ነፃነቱን ማንም ሊቀማው አይገባም ይላል። ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሉዓላዊ መብቱ እንዲከበር፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ባለሙሉ መብትና የሀገሪቱም ባለቤት የሆነው ሕዝቡ ራሱ እንጂ ጥቂት ገዢዎቹ አለመሆናቸው በዘላቂነት እንዲረጋገጥ፤ በሕዝቡ እኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነቱ እንዲለመልምና እንዲጸና፤ ለመታገል ዐልሞ የተነሣ ፓርቲ ነው። ኢሕአፓ ለትምህርት መስፋፋት፥ ለሕዝብ ጤና መጠበቅ፥ ሕዝብ በቂ ምግብ የሚያገኝበትን ሁኔታዎች ለመፍጠር፥ ለቴክኖሎጂ ማደግ፥ ለባሕል መዳበርና መበልጸግ፥ ለሥልጣኔ መስፋፋት በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮና ሕይወት እንዲሻሻልና እንዲያድግ፥ እንዲሁም ሕዝባችን ከፖለቲካ መብት መቀዳጀቱ ጋር ተያይዞ ማኅበራዊ ፍትኅን የሚያገኝበት ሁኔታ እንዲፈጠር፤ ለመታገል የተመሠረተ ድርጅት ነው።

ኢሕአፓ፥ ሀገራችን ኢትዮጵያ፥ ኋላቀር ሥርዓቶችና ብልሹ ገዥዎች መለያዋ ካደረጉት ድኅነት ተላቅቃ፥ እንድትለማና እንድታድግ በመፈለግ፤ ይህንንም ማድረግ ይቻላል ብሎ በማመን፥ ይህንን ራዕይ ይዘው የተነሡ፥ ራዕያቸውንም ታግለው በመሥዋዕትነት ለማስገኘት የቆረጡ፥ ከሦስት አሰርት ዓመታት በፊት ወጣት የነበሩ አብዮታዊ ኢትዮጵያውያንን በማሰባሰብ የተመሠረተ ለዚህም የታገለና ያታገለ፤ በማይታበል ደረጃ ኅልቆ መሣፍርት የሌለው መሥዋዕትነት የከፈለ ባለራዕይ የፖለቲካ ድርጅት ነው።

የኢሕአፓ አባላት ከሕዝቡ አብራክ በመፈጠራቸው ብቻ ሣይሆን የሕዝቡን መሠረታዊ ጥያቄዎች በትክክል በተዓማኒነትና በድፍረት በማንሳታቸውና ለጥያቄዎቹ መመለስም ሳያወላውሉ በጽንዓት በመታገላቸው ነው የሕዝባቸውን ዕምነትና ልባዊ ድጋፍ ያገኙት ወይንም የሕዝባዊነትን ፀጋ የተጎናጸፉት። ለሕዝቡ መቆም ማለት ደግሞ ለነፃነቱ፥ ለክብሩ፤ ለመብቱ፤ ለሥልጣን ባለቤትነቱ፤ ፀንቶ መታገል፤ በቅንነት መታገል፥ አስፈላጊውን መስዋዕትነት መክፈልም ማለት ነውና ኢሕአፓ በላቡና በደሙም ነው እነዚህን በራዕዩ የተካተቱትን መሰረታዊ ዓላማዎቹን ዕውን ለማድረግ የተነሳው፤ እነሆ ዛሬም እየቀጠለ ያለው።

ኢሕአፓ ዛሬም እንደትናንቱ በዕምነቱና በአመለካከቱ ወገንተኛ ነው፤ የሚወግነውም ከሚጨቆኑት፥ ከሚበደሉት፥ ከሚበዘበዙት ላብአደሮችና

አርሶአደሮች፥ ለጉልበታቸውና ለላባቸው ፍትሃዊ የሆነ ክፍያ ከማያገኙት ሠርቶበሌዎች፥ ከተናቁትና ከተዘነጉት የኅብረተሰብ ክፍሎች ፥ የድርብ ጭቆና ሰለባ ከሆኑት ሴቶች፥ ምግብ መጠለያና የትምህርት ዕድል ከተነፈጉት መጠጊያ ካጡት ሕፃናቶች፥ ለሥራአጥነት ከተዳረጉት ወጣቶችና ጎልማሶች ...ወዘተ ... ...በአጠቃላዩም ከሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ነው፡፡ ኢሕአፓ የሚመራበት ርዕዮተዓለምም ሶሻል ዴሞክራሲ ተብሎ በሚታወቀው የአስተሳሰብ አድማስ ክልል የሚካተት ነው፡፡

ኢሕአፓ ፀረ ሠላም የሆኑ የገዥ ሃይሎችን እመቃና ጭቆና በሃይል ጭምር መታገል ተገደደ እንጂ አፍቃሬ ሠላም የሆነ ድርጅት ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሠላም ማስፈንም ከኢሕአፓ ራዕይ አንኳር ሃሣቦች አንዱ ነው፡፡ የኢሕአፓ ፍላጎት የነገዋ ኢትዮጵያ ውስጥ የጥላቻና የበቀል ስሜት ተወግደው የዕርቅና የሠላም መንፈስ ሰፍኖ እንዲታይ ነው፡፡

ጥቂት ጉልበታሞች ከባዕዳን ጋር እየተመሣጠሩ በሚፏልሉበት በዛሬው ዓለማችን ውስጥ የኢትዮጵያውያንም ሆነ የሌሎች ሕዝቦች ነፃነታቸውን መነጠቅ፥ መብታቸው መረገጥ፥ ጥቅማቸው መነፈግ፥ ወይንም ሀገራዊ ኅልውናቸውን የሚያጡበት ሁኔታ መፈጠር የጉልበታሞቹን ፍላጎትና ጥቅም እስካልጎዳ ድረስ የተበቱትንና ተላላኪዎቻቸውን ከቶም የሚያስጨንቃቸውም ሆነ ቅድሚያ የሚሰጡት ጉዳይ አይሆንም፡፡

ስለሆነም የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነቱን ለመቀዳጀት፥ የሀገሩን ኅልውና ለመጠበቅ፥ የሥልጣን ባለቤትነቱን ለማረጋገጥ፥ በእኩልነቱ ላይ የተመሠረተ አንድነቱን ለማስገኘት፥ ለማለምለምና ለማጠናከር፥ሰብዓዊና ዴሞክራሢያዊ መብቶቹን ዘላቂነት ባለው ደረጃ ለመቀዳጀት፥ በአጠቃላይም በችጋር ከመቆላትና በድህነት ከመሮከት፥በከባዱም በቀላሉም ደዌና በሽታ ከመሠቃየትና ከማለቅ የሚላቀቅበትን ሁኔታ ለመፍጠር እንዲቻል ባለፉት አያሌ ዓመታት ውስጥ ካካሄደው ትግል የገበየውን ትምህርት በመጠቀም፤ ለድል ማብቃት የሚገባውን የወደፊቱን ትግሉን በተሻለ መንገድ አደራጅቶና አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡ ይህንንም ለማድረግ እንዲችል ሕዝባዊ ራዕይና የሕዝቡን ትግል ለመምራትም ዝግጁነትና ብቃት ያለው የፖለቲካ ድርጅት ያስፈልገዋል፡፡

የኢሕአፓ ፖለቲካዊ፥ ኢኮኖሚያዊም ሆኑ ማኅበራዊ ፖሊሲዎቹ ማጠንጠኛቸው የሕዝቡን ነፃነት፥ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት እንዲሁም መሠረታዊ ጥቅሞቹን በትክክል መግለፃቸው፥ ማራመዳቸው መጠበቃቸው ወይንም ማረጋገጥ መቻላቸው ነው፡፡

<u>ለመሆኑ ዛሬ የሀገራችን መሠረት የሆነው ሕዝባችን በምን ሁኔታ ላይ ነው ያለው?</u>

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ በሕዝብዋ ብዛት (ከናይጄሪያና ከግብፅ ለጥቃ) ዛሬም ሦስተኛይቱ ሀገር እንደሆነች ይታወቃል። የኢትዮጵያን ሕዝብ ብዛት በተመለከተ የኢሕአዴግ ባለሥልጣኖች በየዓመቱ በ2.7 በመቶ ያድጋል ሲሉን ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት (አይ.ኤም.ኤፍ.) ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር የሚያድገው በዓመት በ2.2 በመቶ ነው ይላል። በዚሁ ዝቅ በሚለው (2.2 በመቶ) ሂሣብ እንኳን የሕዝባችን ቁጥር ቢያድግ ዛሬ ሊኖር የሚገባው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት 73¸654¸526 ነው መሆን ያለበት። ታዲያ ከ73 ሚሊዮን ተኩል የሚበልጥ ሕዝብ የሚኖርባት ኢትዮጵያ ዛሬም ድህነት÷ ረሃብና ልመና በዓለም ሕብረተሰብ ፊት መታወቂያዋ እንደሆኑ ነው ያለችው። የአንድ ኢትዮጵያዊ የነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ገቢ ከአንድ መቶ የአሜሪካ ዶላር በታች እንደሆነ ነው የሚታወቀው። በአንድ ዘ ኢኮኖሚስት ኢንተሊጀንስ ዩኒት በሚል ስያሜ በሚወጣ ጥናት መሠረት ከአሥር ዓመት በፊት በወያኔ አጋፋሪነት ነፃነት ያገኘችው ኤርትራ ውስጥ እንኳን የአንድ ሰው የዓመት የነፍስ ወከፍ ገቢው ሁለት መቶ የአሜሪካን ዶላር ይደርሳል ተብሎ ተገልጧል።

የሕዝብ መጠን ዕድገትን በተመለከተ በ 2.7 ከመቶና በ2.2 ከመቶ መሐል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ቢሆንም ዝቅተኛውን የመረጥነው ያለምክንያት አይደለም። ሁሉም አሁን በሥልጣን ላይ ባለው ቡድን የሚፈበረኩ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ሃቀኛነታቸው ወይም ተዓማኒነታቸው አጠያያቂነቱ እንዳለ ሆኖ÷ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ሕዝባችንን እየጨረሱት ያሉትን በሽታዎቹን÷ ችጋርና ጠኔውን÷ ጦርነቶችንና ግጭቶችን÷ እንዲሁም የመንግሥትን ጭፍጨፋ በበቂ እንደማይገልጣቸው በማወቅ ነው። ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት በሚካሄድባቸው የቴክኖሎጂ እድገት በሚታይባቸውና ማኀበራዊ-ርትዕ የሀገራዊ መርሃ ግብር አካል በሆነባቸው ሀገሮች ውስጥ የሕዝብ ብዛት እንደችግር አባባሽ ጉዳይ ሊታይ አይችልም። ሆኖም ግን በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ የሚባሉት የልማትና ዕድገት ርምጃዎች በጣም አጠያያቂ በሆኑበትና የማኀበራዊ ርትዕ መርሆም ደብዛው በጠፋበት ሁኔታ የሕዝባችን ቁጥር ወይንም መጠን የተናጠል እድገትና ግሽበት በሀገር ውስጥ የሚመረተውን ውሱን ምርትና ሀብት እንዲሁም በብድርና በእርዳታ ከውጭ የሚገኘውን ገንዘብ ለመሻማት ርኩቻን ስለሚጋብዝ÷ በመጠን አነስተኛ የሆኑት ገዢዎች ሃብታሞችና ጉልበታሞች ደግሞ ከዚህ ውሱን ምርት÷ ሃብትና ገንዘብ ውስጥ አብላጫውን ያለጥርጥር መውሰዳቸው ስለማይቀር፤ ከጠቅላላው ሕዝብ አብዛኛውን ወደ ባሰ ችግርና ድህነት መክተቱ የሚጠበቅና እየታየም ያለ ነው። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያኝን በየአመቱ የሚጨምረው ሕዝብዋ ወደ ሁለት ሚሊዮን ይጠጋል። ዋሾው የሕውሃት/ኢህአዴግ መንግሥት በሚያወጣው አሃዝ እንኳን ከሕዝብዋ 44.2 ከመቶው የሚሆነው በከፋ ድህነት አረንቋ ውስጥ ይገኛል ይላል። ታዲያ እነዚህ ከሃቅ የተጣሉ የህወሃት/ኢሕአዴግ ባለሥልጣኖች እንኳን ይህን ያህሉን ማመን ከተገደዱ ቢያንስ ከሕዝባችን ከግማሹ ማለትም 50 ከ 100 ከሚሆነው በላይ በከፋ ድህነት ውስጥ

እየፎከተ የሚኖር ነው ማለት ነው:: በከፋ ድህነት ውስጥ ስላሉት ተናገርን እንጂ ከቀሪው ክፍል ደግሞ ምን ያህሉ በቂ ምግብ÷ ንጹህ የመጠጥ ውሃ÷ መጠለያ÷ የጤና አገልግሎት እንዲሁም ለልጆቹ ትምህርት ወዘተ እንዲሚያገኝ በዝርዝር አልመረመርንም::

የአንድ ሀገር ሕዝብ ብዛትና የመጠኑም እድገት ከሀገሪቱ የተፈጥሮ ሃብት ክምችት መኖርና አለመኖር ጋር ብቻ ሳይሆን ከሕዝቡ ነፃነት መቀዳጀትና አለመቀዳጀት÷ከተንሠራፋው የፖለቲካ ሥርዓት መሠረታዊ ባህሪያት÷ ማለትም ዴሞክራሲያዊ መሆን አለመሆኑና÷ ዜጎች ችሎታቸውንና አፍላቂነታቸውን ነፃ ሆነው ለመጠቀም ከመቻል አለመቻላቸው፤ ከሥርዓቱ መሠረታዊ ፖሊሲዎች ዓይነት በተለይም ከማኅበራዊ ፍትኅ መርሆዎች መኖር ወይንም አለመኖር÷ እንዲሁም በትምህርትና ቴክኖሎጂ እድገት ላይ ትኩረት ከመኖርና አለመኖር÷ ከልማት አውታሮች ከህዝቡ ብዛት ጋር በተመጣጣኝ ደረጃ መኖር አለመኖር÷ በተለይም ከትምህርት ቤቶች በብቃት መኖር አለመኖር÷ ከጤና ተቋሞች በበቂ መኖር አለመኖር÷ ከኢኮኖሚው ዕድገት ፍጥነትና እሱም ካለው ሥራን የመፍጠር ችሎታ ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚገባው ነው እንላለን::

ሕዝባችን በቂ ምግብ ሊያገኝ ይገባል÷ ወላጅ እናቶች አልሚ ምግብና ሕክምና ካላገኙ ልጆቹ ጤናማ ሆነው አያድጉልንም÷ አብዛኛው ሕዝብ መሐይም ከሆነ የቤተሰቡን ዕድገት በዕቅድ መሠረት ለማድረግ አይቻልም:: ስለዚህ ወላጆች ወይንም የቤተሰብ ሃላፊዎች ሊያሳድጓቸው ከሚችሉት በላይ ይወልዳሉ ማለት ነው:: ከበዙ ደግሞ በምግብ በጤናም በቂ ክብካቤ አያገኙም:: በርካታዎቹ በሕፃንነታቸው አለዚያም አምስት ዓመት እንኳን ሳይሞላቸው እንደቅጠል ይረግፋሉ:: ያልቃሉ:: ወባ ብቻውን የሚፈጃቸው ሕፃናት ቁጥራቸው እጅግ ብዙ ነው:: ተርፈው ከሚያድጉት የደሀ ኢትዮጵያውያን ልጆች መሐል አብዛኛዎቹ ተጎድተውና ቀጭጨው ነው የሚያድጉት:: ታዲያ ቀሳፊው የዘመኑ በሽታ ከተለመዱት ሕዝቡን ሲመደምዱ ከኖሩት ጋረ ተዳምረው የሀገራችን ዋና ሃብት የሆነውን ሕዝባችንን ክፉኛ ይፈታተኑታል::

የአገራችን ህልውና÷ ልማት÷ እድገትና ብልጽግና መሠረቱ ሕዝብዋ ነው:: የሰው ኃይል ሁለንተናዊ አቅምና ጉልበት በተገቢው ትምህርትና ሥልጠና መኮትኮት÷ በቀጣይነት የሀገሪቱን ፍላጎት ሊያረካ በሚችል ደረጃም ማሳደግ÷ መንከባከብና ይህንኑ የሰው ሃይል በሀገሩ ውስጥ በፍላጎቱና ነፃ ሆኖ እንዲቀይና ትምህርቱን÷ ዕውቀቱንና ችሎታውንም በሥራ ላይ ለማዋል እንዲችልም ሁኔታዎችን መፍጠር ያስፈልጋል:: አለዚያ አንዲት ሀገር ወደፊት መራመድ ይሣናታል::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለፉት ሰላሳ ዓመታት በታሪኩ ታይቶ ባልታወቀ ደረጃ እንደ ኤች.አይ.ቪ. ባለ ዘመናዊ ቀሣፊ በሽታና መረን በለቀቀ የወባ በሽታ መስፋፋት እያለቀ ከመሆኑም በተጨማሪ ሀገሪቱ የሰለጠነ የሰው

ኃይሏን በፍልሰትና በስደትም የተነሳ በብዛት እያጣችም ነው፡፡ በሕዝብ ወጪ በከፍተኛ ደረጃ የተማሩና የሰለጠኑ፥ ሌሎችንም በማስተማርና በማሠልጠንም ላይ ያሉ፥ ሌክቸረሮችና ፕሮፌሰሮች፥ ሐኪሞች፥ ነርሶች፥ አይሮፕላን አብራሪዎች፥ መሃንዲሶች፥ የባንክ ባለሙያዎች፥ የኤኮኖሚ ጠበብት፥ ከያንያን፥ ሳይቀሩ-ወደ መካካለኛው ምሥራቅና ወደ ምዕራቡ ዓለም፥ ወደ አውስትራሊያ፥ ኒው ዚላንድና ደቡብ አፍሪቃ፥ ወዘተ.... ተሰደዋል፡፡ ይህ ፍልሰትና ስደት ዛሬም በከፋ መልክ እንደቀጠለ ነው፡፡ ይህ ቀጣይ ክስተት እየሆነ የመጣ የመሰደድ ውርጅብኝ በአገሪቷ ኤኮኖሚያዊና ማኅብራዊ ኅላዌና ሕይወት ላይ አሽመድማጅ ውጤት እንዳለውም ግልፅ ነው፡፡ የጥፋት መልክተኛ የሆነው የወያኔ ኢሕአዴግ መንግሥት በይፋ ባያምንም የአገሪቷን ተቋሞች ሃላፊነታቸውን የመወጣት አቅምና ችሎታቸውንም ያለጥርጥር ጎድቷል፡፡

ምዕራባውያን ደግሞ ከተለያዩ ደሀ ሀገሮች እየፈለሱ በሚመጡ ባለብሩሕ ዓዕምሮዎች እየተጠቀሙ ስለሆነ የሚለሙትና የሚያድጉት በኢትዮጵያ ላይ እንደመቅሠፍት የወረደውን ፍልሰትም ለራሳቸው ጠቃሚ ሆኖ ስላገኙት አልተቃወሙትም፡፡ እኛስ “ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል” እንል የለ፡፡ ይህም ሆኖ ደግሞ እነዚሁ ገንዘብ አበዳሪና እርዳታ ሰጪ የምዕራብ አገሮች ኢትዮጵያ ከድህንት መላቀቅ የምትችለው በርካታ የተማረ የሰው ኃይል ሲኖራት ነው ብለው ይሣለቁብናል፡፡

ለምን የተማረውና የሰለጠነው ኃይል ይሰደዳል የሚለውን ጥያቄ ማንሳታችን የግድ ይሆናል፡፡ የውጭ እርዳታ እየጠየቅን በሌላ በኩል ደግሞ ለአገር እድገት እውን መሆን ወሳኝ የሆነውን ችሎታ ያለውን የሰው ኃይል ማጣት ጥሩ ዓዕምሮ ሊቀበለው የሚችል ጉዳይ አይደለም፡፡ ከውጭ የሚገኘው ማንኛውም ዓይነት እርዳታ ሀገሪቱ ያፈራችውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በአገር ውስጥ አቆይቶ በየሥራ ዘርፉ በማሰማራት ከሚገኘው ጥቅም ጋር በፍፁም ሊወዳደር አይችልም፡፡

የዓለም የሰራተኞች ድርጅት (አይ.ኤል.ኦ) እንዳቀረበው ከሆነ (እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር) በ1980ዎቹ ዓመታት ወደ ውጭ አገር ለትምሕርት ከተላኩት ኢትዮጵያውያን ውስጥ 77 በመቶው በወጡበት ቀርተዋል፡፡ ኢትዮጵያ በኤድስ፥ በወባ፥ በተስቦ፥ በሳንባ ነቀርሣ፥ ወዘተ.... በሽታዎች በከፍተኛ ደረጃ ከተጠቁት አገሮች አንዷ ናት፡፡ ይኸ አሰቃቂ ዕውነታ እያለ ከ1980 እስከ 1991 (በአውሮጳውያን አቆጣጠር) 33 በመቶ ሐኪሞቿ አገር ጥለው ሄደዋል፡፡ አንድ በቅርብ የወጣ ዘገባ እንዳቀረበው በአሜሪካ አንዲቷ ከተማ ቺካጎ ውስጥ ያሉ ኢትዮጵያውያን ሀኪሞች ቁጥር በኢትዮጵያ ካሉት ሀኪሞች ቁጥር ይበልጣል ብሏል፡፡ አምሳ ሽህ ሰው ለማከም አንድ ሃኪም ብቻ ያላት ኢትዮጵያ ሃኪሞቿንና የጤና ባለሙያዎቿን ማጣት በውነቱ ይቅርታ የማይደረግለት በደል ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከጋናና ናይጄሪያ ቀጥላ ሀኪሞቿ ወደ ባዕድ የሚሰደዱባት ሶስተኛ የአፍሪካ ሀገር ናት፡፡ ይህ አሳሳቢ ክስተት መቀጠል የለበትምና

የተማረ የሰው ኃይል ለምን ከሀገር ይወጣል ለሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ምላሽ መስጠት ይኖርብናል፡፡ ይኽን ጎጂ ክስተት በተመለከተ ዋና ዋና መንስዔዎቹን መመርምር አለብን፡፡

ስደትና ፍልሰቱ የተከተለው ያለምክንያት አይደለም፡፡ ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥ፡-

1. በፖለቲካዊ ምክንያቶች በሀገሪቱ ውስጥ የሰላምና የደህንነት መጥፋት ፥ በነፃነት ለመኖርም ሆነ ለመሥራት አለመቻል፥ የመብቶች አለመከበር፥
2. እየሰሩ የመጣና አመርቃዥ የሆነ ሥራ አጥነት መኖር፤ ሆን ተብሎ የሥራ መስኮችን ለመፍጠር የሚደረግ እንቀስቃሴ ውሱንነት ወይንም አለመኖር፥ትምሕርታቸውን የጨረሱ ወጣቶች ወይንም ለዓመታት ሥራ አያገኙም ወይም የሚገባቸውን ክፍያ አያገኙም፡፡ ሥራ ለሚያገኙትም ቢሆን የደሞዝ ክፍያው ዝቅተኛ መሆኑና አስፈላጊ ተጓዳኝ ጥቅሞች አለመኖር፥
3. በግለሰብ ደረጃ የራስን ሥራ ለመፍጠር አበረታች ሁኔታዎች አለመኖር፥ በንግድ የመሰማራት ዕድል ውሱንነት፥ ተበድሮ የራስን ሥራ ለመጀመር በጣም አስቸጋሪ መሆኑ፥
4. ደካማ የጤና እንክብካቤ፤የትምህርት ዕድልና የህብረተሰብ ግልጋሎት መኖሩ፥
5. ሙስና፥ የሕግ የበላይነት አለመኖር፥ በአድልዎ የሚሠራበት ሁኔታ መስፈኑ ለአብነት የሚጠቀሱ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ስለዚህም አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ተሰደው ሌላ ቦታ፥ በሌሎች ሀገሮች ውስጥ በሰላም መኖርን፥ ሥራ ማግኘትንና የተሻለ ክፍያን መፈለግ ይገደዳሉ፡፡ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት በሚከተለው የተማረውንና የሰለጠነውን የሰው ኃይል በመሠረተቢስ ውንጀላዎች የማግለል ፖሊሲው ምክንያት፥ ለምሳሌ በአስተማሪዎች፥ፕሮፌሰሮች እንዲሁም ሃኪሞች ላይ የወሰዳቸው የማባረር ርምጃዎቹ፥ ለተማረው ኃይል መሰደድ አስተዋፅዖ አድርጓል፡፡ ችሎታ ያላቸውን ኢትዮጵያውያን ከሥራ እያባረሩ ወይም የሥራ ዕድል እየነፈጉ በአንፃሩ በከፍተኛ ክፍያ ባዕዳንን መቅጠር ምንም ዓይነት አሳማኝ ምክንያት ሊገኝለት የማይችል አሳፋሪ ድርጊት ነው፡፡

“ከግፍም ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮደግፍ” እንደሚባለው ሆነና ኢትዮጵያ በኋላ ቀርነትዋና እንደድርቅ ባሉት ተፈጥሮአዊ ምጣቶች ተደጋግሞ ከመመታትዋ በተጨማሪ የብልሹ ሥርዓቶችም ሠለባ ሆና ነው የኖረችው፡፡

በአንድ ሀገር ከሚኖር ሕዝብ፥ በተለይም ነፃነቱን ተቀምቶ በአምባገነናዊ ሥርዓት ውስጥ ከሚማቅቅ ሕዝብ፥ አብዛኛው ከደንታቢስ ገዥዎች፥ ከጉልበታሞችና ከሃብታሞች ምዝበራና ዘረፋ የሚተርፈውን ምርት፥ ሃብት፥ ግልጋሎት ወይንም ገንዘብ ተቋድሶና ተቃምሶ መኖር ስለሚገደድ

ነው የድህነትን ማቅ አጥልቆ የሚኖረው፡፡ ድህነት ለጤና መጓደል ይዳርገዋል፡፡ የጤናው መጓደል ደግሞ የመሥራትና የማምረት አቅም ያሳጣዋል፡፡ እኒህ ሁለቱ የተያያዙና የተቆራኙ ናቸው፡፡ ድህነትን ለማስወገድ የምንችለው በግድ ለድሀው ሕዝብ ያለውን የጤና አገልግሎት ይዞታና ሁኔታ ማሻሻልና መለወጥ ስንችል ነው፡፡ አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የጤና አገልግሎት ይዘት ስንመለከት ብዙሃኑ የገጠር ነዋሪ ሕዝብና በከተሞች ውስጥም የሚኖረው ድሃው ወገናችን ጭምር መሠረታዊ የጤና አገልግሎት አያገኙም፡፡ የጥናት ውጤቶኘ አሃዞኘ ይህንኑ ይበልጥ ግልፅ ያደርጉታል፡፡

በ2002 ዓ.ም. "ድህነት በኢትዮጵያ" በሚል የተካሄደ ጥናት በሀገራችን ውስጥ ያኔ ለነበረው 72 ሚሊዮን ሕዝብ 86 ሐኪም ቤቶች ብቻ መኖራቸውንና ለ 15 ሽህ ሰው አንድ ነርስ ብቻ እንዳለ አሳይቷል፡፡ ካሉት ሐኪሞችም 62 በመቶው በአዲስ አባባ የተከማቹ መሆናቸውም ተገልጦ ነበር፡፡ በመሆኑም ስድሳ በመቶው የገጠር ሕዝብ ሲታመም ሕክምና አያገኝም ነበር፡፡ በገጠር የነበረው የጤና አገልግሎት ደግሞ በአብዛኛው በመንግሥት የሚሰጥ ሳይሆን በግል ጥረቶች፥ በግብረሰናይ የሰብዓዊና የሐይማኖት ድርጅቶች፥ ወዘተ.... የሚካሄድ ነበር፡፡ እነዚህ ተቋሞች በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ውስጥ 1700 ክሊኒኮችን ከፍተው እየሠሩ ነበር፡፡ በገጠር ኢትዮጵያ ሕዝቡ ያለው የመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ፍላጎት በጣም ከፍተኛ ሰለሆነ ከማንኛውም ለሕዝብ የሚቀረቀር ሃይልና መንግሥት አስቸኳይ ምላሽን የሚጠይቅ ፍፁም አንገብጋቢ ጥያቄ ነው፡፡

ትምሕርት አዲሱን ትውልድ በየወቅቱ ማንነቱን እንዲያውቅ ለማድረግ የሚረዳ መሣሪያ ነው፡፡ በባዕዳን ለራሳቸው ሀገርና ሁኔታ የተዘጋጁና የተፃፉ መጽሐፍት፥ በባዕዳኑ አማካይነት የትምህርት መስጫ ከተደረጉ ኢትዮጵያዊ ማንነትን፣ ትክክለኛ ታሪክን፣ በሚማሩት ወጣት ኢትዮጵያውያን ዓዕምሮ ውስጥ አያሠርጹም፡፡ ስለሀገራችንም ችግሮች ወጣቶቹን አያሳውቋቸውም፡፡ ስለዚህም ነው ትምህርት ከአንድ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ፥ የዕድገት ደረጃ፥ ወዘተ ጋር የተሣሠረ ነው የምንለው፡፡ የትምሕርት ፖሊሰዎችና ፕሮግራሞች ሲቀረጹ የኅብረተሰቡን ሁኔታዎች ያገናዘቡ፥ በሕዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎና አስተዋፅዖ ላይ የተመሰረቱ ካልሆኑ፣ ማኅበራዊ ፍትኅ መርሆ ላይ በመመሥረት በተለይ ከድሀ ቤተሰብ የሚመጡ ተማሪዎች ትምሕርትና የትምሕርት ቁሳቁስን በነፃ ማግኘት የሚያስችሏቸው ካልሆኑ፥ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ማለትም ኮሌጆች፣ ዩኒቨርስቲዎች፣ የምርምር ተቋሞችና ማዕከሎች ሌሎችም የማሠልጠኛ ተቋሞች መማር ለሚፈልጉ ችግረኞች የደሃ እትዮጵያውያን ልጆች ነፃ ካልሆኑ፥ ትምሕርት የአንድ ሀገርን ችግር ለመፍታት አያስችልም፡፡ በተለይም ትምህርት እንደኢትዮጵያ ባሉ የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ወሣኝ ሚና በሚጫወትባቸው ሀገሮች ለገጠሩ ክልልና ለእርሻው መስክ አስፈላጊውን ትኩረት የሚሰጥ ካልሆነ ፣ የትምህርት ተቋሞች ለእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ በቂ የተማረና የሠለጠነ

የሰው ኃይል የማያፈሩና ድጋፍ የማይሰጡ ከሆኑ ሀገሪቷን ለማልማትና ለማሳደግ አይረዳም።

ስለሀገራችን የፖለቲካ ሁኔታና በአሁኑ ወቅት ስላለው እንቅስቃሴ፣ ስለ ኢኮኖሚ ልማትና ዕድገትም ሆነ ስለማኅበራዊ ችግሮች መወገድ ወደ ዝርዝር ጉዳዮች ከመግባታችን በፊት የመሠረታዊ ጉዳዮች ተዛማጅነት ትስስርና ቁርኝት እንዳለ መገንዘብ ያስፈልጋል። መሠረታዊ የሆኑት ችግሮቻችን ጠንካራ ቁርኝት ስላላቸው ሌሎችን ተዛማጅ የሆኑትን አብረን ሳንዳስስ አንደኛውን ብቻ ለመፍታት መሞከር የሚፈለገውን ዕድገትና ልማት አያስገኝልንም። ስለዚህም ሁሉንም በተናጠል ለመመልከት ስንሞክር ተዛምዶአቸውንም እያገናዘብን ሊሆን ይገባል ።

ይቀጥላል።

<u>ማስታወሻ</u>

ይህ ጽሁፍ በኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ ለአራተኛው የኢሕአፓ ጠቅላላ ጉባኤ የተዘጋጀ ሲሆን በአቶ ሰለሞን ገብረ ስላሴ ትብብር ለፍኖተ ዴሞክራሲ ሬዲዮ ዝግጅት በሚቀርብ መልኩ እንደገና ተዘጋጅቶና በፍኖተ ዴሞክራሲ ኢዲቶሪያል ቦርድ ታርሞ የቀረበ ነው።